

# ክትትልዎን ይቀጥሉበት!



## ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን፣ ልጅዎ ክትባታቸውን በወቅቱ ማግኘታቸው አስፈላጊ ነው።

## አዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች - የትምህርት ቤት የክትባት መስፈርቶች

የዲስትሪክት ህግ[1] እና ደንቦች[2] በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ ትምህርት ቤቶች ተማሪው የህጻናት የክትባት መስፈርቶችን[3] ያሟሉ መሆኑን እንደ አንድ የምዝገባ እና የመማር ቅድመ ሁኔታ እንዲያጣሩ ያስገድዳል። ተማሪው ግዴታውን ካላሟላ፣ትምህርት ቤቱ የጎደለውን ክትባት(ቶች)ን በሚመለከት ወዲያውኑ በጽሁፍ ለወላጅ፣ሞግዚት፣ወይም አካለመጠን ለደረሰ ተማሪ እንዲያሳውቅ ይገደዳል። ተማሪው በ20-የትምህርት ቀን ጊዜ ውስጥ ግዴታውን ካላሟላ፣ትምህርት ቤቱ የክትባቱ ሰርተፊኬቱ እስኪደርሰው ድረስ ተማሪውን በአካል ከሚደረግ ትምህርት ማገድ አለበት።

### 1. ክትባቶች አስፈላጊ የሚሆኑት ለምንድን ነው?

በርካታ ተላላፊ በሽታዎች፣እንደ ኩፍኝ የመሳሰሉ በከፍተኛ ሁኔታ የሚተላለፉ እና በእድሜ አነስተኛ ለሆኑ የዲስትሪክቱ ኗሪዎች አደገኛ ናቸው። የእነዚህን ተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት ለመከላከል፣ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፊት ሙሉ በሙሉ መከተባቸው ወሳኝ ነው። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከሎች (CDC) ስለክትባት ማወቅ ያለብዎ ስድስት ነገሮች፣[4] የክትባት ውሳኔ ማድረግ የሚሉትን ጨምሮ ስለ ክትባቶችን አስፈላጊነት ግብዓቶች አለው። HPVን በሚመለከት የተለመዱ ስጋቶች ፣[5]እና ፍሬ ነገሮችን መፍታት።[6]

### 2. ለኔ ልጅ የሚያስፈልጉ ክትባቶች የትኞቹ ናቸው?

መስፈርቶቹ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ጤና መምርያ የተዘጋጁ እና የልጁን እድሜ መሰረት ያደረጉ ናቸው።[7] ስለሚያስፈልጉ ክትባቶች ዝርዝር፣የDC Healthየክትባት መስፈርቶችን ይመልከቱ።[8]

### 3. ልጄ የትኞቹን ክትባቶች አስቀድሞ የወሰደ መሆኑን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ስለልጅዎ የክትባት ታሪክ ጥያቄዎች ካሉት፣የጤና አቅራቢዎን ያግኙ እና የልጅዎን የክትባት ታሪክ ቅጂ ይጠይቁ ወይም የDC Health የክትባት ፕሮግራም ጋር በ(202) 576-7130 ይደውሉ።

### 4. ልጄ መከተቡን የልጄ ትምህርት ቤት እንዴት ያውቃል?

አንድ ልጅ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ከተከተበ፣የጤና አቅራቢው የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች እና ጎብኚዎችን የክትባት መረጃን ወደሚከታተለው የዳታ ሲስተም፣የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የክትባት የመረጃ ሲስተም (DOCIIS) ውስጥ ይጨምረዋል። ትምህርት ቤቶች የክትባት መስፈርቶች መተግበራቸውን ለመከታተል DOCIIS ይከታተላሉ። በተጨማሪ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤት የጤና መዝገብ ላይ የልጅዎን የክትባት ሪከርድ የጽሁፍ ሪከርድ ሊይዙ ይችላሉ። ማስታወሻ፥ ልጅዎ የተከተቡት ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውጪ ከሆነ፣በDOCIIS.ውስጥ ላይታይ ይችላል።

### 5. የልጄን የክትባት ማስረጃ ለልጄ ትምህርት ቤት እንዴት ማቅረብ እችላለሁ?

ልጅዎ አስፈላጊውን ክትባቶች መውሰዱን DOCIIS የማያሳይ ከሆነ፣ትምህርት ቤትዎ የክትባት ማስረጃ ይጠይቃል። የልጅዎን የክትባት ማስረጃ እንደ ዓለምአቀፍ የጤና ሰርተፊኬት (ተመራጭ) ወይም የአቅራቢውን ኦፊሺያል ማህተም ወይም ፊርማ ያለው ከጤና አቅራቢዎ ሌላ ኦፊሺያል ሪከርድ ያቅርቡ።[9] ትምህርት ቤቱ ይህ ሰነድ በDOCIIS ውስጥ መግባቱን እና የልጅዎ ትምህርት ቤት የጤና መዝገብ ውስጥ መካተቱን ያረጋግጣል። ከጤና አቅራቢ የሚሰጥ የቀጠሮ ካርድ የክትባት ማስረጃ መስፈርቶችን አያሟላም።

### 6. ልጄ ሁሉም ክትባቶችን ካልወሰደ፣ትምህርት ቤት መከታተል ይችላሉ?

ተማሪዎች የክትባት ማስረጃ ሳይዙ ትምህርት ቤት መከታተል የሚችሉት ለ20 የትምህርት ቀናት ብቻ ነው።[10] ትምህርት ቤቱ ልጅዎ አስፈላጊ ክትባቶችን እንዳልወሰዱ ከወሰነ፣የክትባት ማስረጃ ለማቅረብ 20 የትምህርት ቀናት እንዳሎት ካልሆነ ግን ልጅዎ አስፈላጊውን ክትባት ወስዶ ይህን የሚያሳይ ሰነድ ለትምህርት ቤቱ እስኪያቀርብ ድረስ በአካል ትምህርት ቤት እንዲመጡ የማይፈቀድላቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ወደ ቤት ይልካል።

### 7. ልጄ አስፈላጊውን ክትባቶች ሁሉንም ካልወሰዱ ምን ይፈጠራል?

ትምህርት ቤቶች ግዴታቸውን ያላሟሉ ተማሪዎችን እና የጎደሉ ክትባቶችን በመለየት እና የሚፈለጉትን ክትባቶች ማስረጃ ለማቅረብ 20 የትምህርት ቀናት እንዳሎት የሚገልጽ ማስታወቂያ ወደ ቤት ይልካሉ። የጽሁፍ ማስጠንቀቂያው እንደደረሶት ወዲያውኑ የልጅዎ የጤና አቅራቢ ጋር ቀጠሮ መያዝ አለብዎ።

የክትባት ማስረጃው ለትምህርት ቤቱ በ20 የትምህርት ቀናት ካልቀረበ፣ልጅዎ የሚፈለገውን ክትባት ወስደው ሰነዱን ለትምህርት ቤት እስኪያቀርቡ ድረስ በአካል ትምህርት ቤት እንዲመጡ አይፈቀድላቸውም።

ልጅዎ በርቀት ትምህርት አማካኝነት ትምህርት እንዲያገኝ ይደረጋል ወይም የክትባቱ ማስረጃ ለትምህርት ቤቱ እስኪቀርብ ድረስ ለእያንዳንዱ ቀሪ የሆነበት የትምህርት ቀን "ያለፍቃድ ቀሪ" ይደረጋል። ትምህርት ቤቱ የክትባቱ ማስረጃ ሲደርሰው፣ልጅዎ በአካል ለመማር እና ለሌሎች እንቅስቃሴዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ ይፈቀድላቸዋል እና እያንዳንዱ ቀሪ የሆነበት ቀን "በፍቃድ ቀሪ" ተብሎ እንደገና ይመደባል።

### 8. ልጄ ሁሉንም የሚፈለጉ ክትባቶችን እንደወሰደ ካመንኩ ፣ነገር ግን እና ትምህርት ቤቱ ልጄ አንድ ወይም ከዚያ በላይ እንደጎደለው ቢነግረኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ልጅዎ የሚፈለገውን ክትባት(ቶች) መውሰድ ወይም አለመውሰዱን ለማረጋገጥ የልጅዎን የጤና አቅራቢ ያግኙ። የልጅዎ የጤና አቅራቢ ልጅዎ ክትባቱን(ቶቹን) መውሰዱን ካረጋገጡ፣ለትምህርት ቤቱ የሚሰጡት የጽሁፍ የክትባት(ቶች) ማስረጃ እንዲሰጥዎ ይጠይቁ። ይህ የጽሁፍ ማስረጃ የጤና አቅራቢውን ኦፊሺያል ማህተም ወይም ፊርማ ማካተት አለበት።

የጤና አቅራቢው ልጅዎ የሚፈለገውን ክትባት(ቶች) አለመውሰዱን ካሳወቆት፣በተቻለ ፍጥነት ልጅዎ ክትባቱን(ቶቹን)እንዲወስድ ቀጠሮ ያስይዙ። በቀጠሮው ወቅት፣የጤና አቅራቢዎ የዓለምአቀፍ የጤና ሰርተፊኬት(ተመራጭ) እንዲሞሉ ያድርጉ ወይም የአቅራቢውን ኦፊሺያል ማህተም ወይም ፊርማ ያለው ሌላ ዓይነት የጽሁፍ ማስረጃ ያቅርቡ።[11] ሰነዶቹ የትምህርት ቤቱ የጤና መዝገብ ውስጥ እንዲካተቱ ለልጅዎ ትምህርት ቤት ያቅርቡ።

### 9. ልጄ መከተብ የማይችል ቢሆን ምን ይሆናል?

በህክምና ምክንያት እንዳይከተቡ ለሚመከሩ ህጻናት ከህክምና ግዴታ ነጻ መሆን አለ። ከህክምና ግዴታ ነጻ በሀኪም፣ወይም በተወካያቸው፣ወይም በህዝብ ጤና ባለስልጣን መፈረም አለበት። በሀይማኖት ምክንያት ከግዴታ ነጻ ለመሆን ጥያቄዎን በኢሜይል ለdoh.immunization@dc.gov በማቅረብ ማግኘት ይቻላል። በተጨማሪ የDC Health ዓመታዊ ሂዩማን ፓፒሎማቫይረስ (HPV) ክትባት ግዴታ ነጻ ሰርተፊኬት ለትምህርት ቤቱ[12] በማቅረብ ልጅዎን ከHPV ክትባት ግዴታ ነጻ ማድረግ ይችላሉ።

### 10. ለልጄ ላገኝ የምችለው የቀደመ ቀጠሮ የትምህርት ዓመቱ ከጀመረ በኋላ ከሆነስ?

የጤና አቅራቢዎች በትምህርት ዓመቱ መጀመርያ ላይ ሥራ ሊበዛባቸው ይችላል። ልጅዎ የትምህርት ዓመቱ ከመጀመሩ በፊት የሚፈለጉትን ሁሉንም ክትባቶች ማግኘቱን ለማረጋገጥ አስቀድመው ያቅዱ። የህጻንነት የክትባት ሥፍራዎች ዝርዝር በDC Health ድረገጽ ይገኛል።[13]

### 11. እኔ ቀዳሚ የእንክብካቤ አቅራቢ ወይም የህክምና መድን ከሌለኝ ምን ይሆናል?

እርስዎ ቀዳሚ የእንክብካቤ አቅራቢ ወይም ሀኪም ከሌሎት፣አቅራቢያዎ ያለን ለማግኘት የመድን ኩባንያዎ ጋር ይደውሉ። እርስዎ የህክምና መድን ከሌሎት፣የDC Health Link ያግኙ ወይም 3-1-1 ጋር በመደወል Citywide(ከተማአቀፍ) የጥሪ ማዕከልን ያግኙ።[14]

### 12. ሌላ አገር የተገኘ የክትባቶች ሰነድ ካለኝ ምን ይሆናል?

ልጅዎ ክትባታቸውን የወሰዱት ሌላ አገር ከሆነ፣ስለ ሰነዱ ያሎትን ጥያቄዎች ለትምህርት ቤቱ ነርስ ወይም የትምህርት ቤቱ የክትባት ተጠሪ (IPOC) ያቅርቡ። እነሱ ሰነዱ የክትባት ግዴታን ለማረጋገጥ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ለመወሰን ከDC Health ጋር ይሰራሉ።

### 13. እኔ ትምህርት ቤት በአካል ለመማር ወይም ለሌሎች እንቅስቃሴዎች ስለሚያስፈልገው የክትባት ወይም የክትባቶች መስፈርቶች ጥያቄዎች ካለኝስ?

ስለ ክትባቶች እና ስላሉት ግብዓቶች ጥያቄዎች፣የDC Health የክትባት ፕሮግራምን ያግኙ (https://dchealth.dc.gov/immunizations ) ወይም ይደውሉ (202) 576-7130. በአካል ለመማር ስላለው የክትባት ፖሊሲ፣የትምህርት ቤትዎን ወይም የአካባቢውን የትምህርት ኤጀንሲ(LEA) ማዕከላዊ ቢሮን ያግኙ። በተጨማሪ OSSE በ OSSE.SchoolHealth@dc.govማግኘት ይችላሉ።[15]

ይህ አዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና መልሶች
ከጊዜ በኋላ ይሻሻላል።
በመጨረሻ የተሻሻለበት ቀን፣ ማርች 15, 2021።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1 DC Official Code § 38–501 et seq፣ code.dccouncil.us/dc/council/code/titles/38/chapters/5/
2 DCMR 5-E § 5300 et seq.፣ dcregs.dc.gov/common/dcmr/rulelist.aspx?ChapterNum=5-e53&chapterid=258
3 dchealth.dc.gov/service/school-health-services-program
4 cdc.gov/vaccines/vac-gen/vaxwithme.html
5 cdc.gov/vaccines/parents/why-vaccinate/vaccine-decision.html
6 cdc.gov/vaccines/parents/diseases/hpv.html?CDC_AA_refVal=https%3A%2F%2Fwww.cdc.gov%2Fvaccines%2Fparents%2Fdiseases%2Fteen%2Fhpv.html
7 DCMR 22-B §§ 130-152፣ dcregs.dc.gov/Common/DCMR/RuleList.aspx?ChapterNum=22-B1&ChapterId=576
8 dchealth.dc.gov/service/school-health-services-program
9 dchealth.dc.gov/service/school-health-services-program
10 DC Official Code § 38–505፣ code.dccouncil.us/dc/council/code/sections/38-505.html
11 dchealth.dc.gov/service/school-health-services-program
12 dchealth.dc.gov/node/112212
13 dchealth.dc.gov/service/school-health-services-program
14 dchealthlink.com/
15 osse.dc.gov/page/district-columbia-immunization-attendance-policy

OSSE
DC HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR